# የዕቃ ፍተሻ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 58/2003

የሀገሪቱ የወጪና ገቢ ዕቃዎች እንቅስቃሴ እያደገ የመጣ በመሆኑ እና ወደፊትም በዚሁ ፍጥነት ዕድገቱ እንደሚቀጥል ግምት በመውሰድ ከዕድገቱ ጋር የተጣጣመ ዘመናዊ የዕቃ ፍተሻ አሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ቀረጥና ታክስ በአግባቡ መሰብሰብና የጉምሩክ ወንጀሎችን መከላከል አስፈላጊ በመሆኑ፤
በገቢና ወጪ ዕቃዎች ላይ በሚደረግ ፍተሻና ቁጥጥር ምክንያት የሚባክነውን ጊዜ፣ በዕቃዎች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለማስቀረትና ቁጥጥሩን በአስተማማኝ ሁኔታ ማከናወን የሚያስችል በመሳሪያ የሚታገዝ ፍተሻ በማከናወን በሰው የሚደረግ አካላዊ ፍተሻን መጠን መቀነስና መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፣

በተጨማሪም የዕቃ ፍተሻ አፈፃፀም መመሪያ ከሌሎች የወጪና ገቢ ዕቃዎች ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም መመሪያዎች ጋር የተጣጣመ እንዲሆንና አስቀድሞ በነበረው መመሪያ የነበረውን ችግር ለማስወገድ፣

እንዲሁም የሚኒስትሮች ም/ቤት ሐምሌ 8 ቀን 1997 ዓ.ም. ባካሄደው 136ኛ መደበኛ ስብሰባ በወሰነው መሠረት በዕቃዎች መፈተሻ መሳሪያ ለሚከናወን ፍተሻ የአገልግሎት ክፍያ የሚሰበሰብበት ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 18/10 ስለ ዕቃዎችና ሰነዶች ምርመራ መመሪያ እንዲያወጣ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

   ይህ መመሪያ "የዕቃ ፍተሻ አፈፃፀም መመሪያ" ቁጥር 58/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጉም

   1. "አስተዳደራዊ ውሳኔ" ማለት ባለሥልጣኑ በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የጉምሩክ ወንጀሎችን በፍ/ቤት ክስ መመሥረት ሳያስፈልግ በአጥፊዎች ላይ የሚሰጥ አስተዳደራዊ ውሳኔ ነው፡፡

2. “የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ” ማለት በገቢና ወጪ ዕቃ ሳይ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የሚፈፀምበትና ታክስ የሚሰበሰብበት በቅ/ጽ/ቤት ሥር የሚተዳደር ጣቢያ ነው፡፡

3. “ቅርንጫፍ ጽ/ቤት” ማለት በክልል ወይም በከተማ አስተዳደር የሚገኝ የባለሥልጣኑ ተጠሪ ጽህፈት ቤት ነው፡፡

4. “የመንግሥት መ/ቤት” ማለት በመንግሥት በጀት የሚተዳደርና አትራፊ ያልሆነ ተቋም ነው፡፡

5. “ስታንዳርድ ዝርዝር የዕቃ መግለጫ” ማለት በዲክላራሲዮን ላይ ስለተመዘገቡት ዕቃዎች ዝርዝር ያስተሻሽግ ሁኔታ፣ የዕቃዎች ብዛት፣ የተሰራበትን ማቴሪያል፣ የዕቃውን ዓይነት፣ የተመረቱበትን ሀገር፣ ወዘተ በየዕቃው ዓይነት በመለየት የሚገልፅ ሰነድ ነው፡፡

6. “የሥጋት ደረጃ ቀይ፣ ቢጫ ወይም አረንጓዴ” ማለት እንደቅደም ተከተሉ ከፍተኛ፣መካከለኛ ዝቅተኛ የሥጋት ደረጃ ተብለው በተለዋጭ የሚገለፁት ናቸው፡፡

7. “አዋጅ” ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ነው፡፡

8. ሌሎች ቃላትና ሐረጐች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ወደ አገር በሚገቡ በተሳሳፊ ወይም ከአገር በሚወጡ ዕቃዎች ሳይ ለሚደረግ ፍተሻ እና ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ሰዎች ሳይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>በዕቃ መፈተሻ መሳሪያ ስለመፈተሽ</u>

4. <u>መርህ</u>

በዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 ከተዘረዘሩት ዕቃዎች ውጪ ያሉ የሥጋት ደረጃቸው ከግምት ውስጥ ሳይገባ ማናቸውም ገቢና ወጪ ዕቃዎች በዕቃ መፈተሻ መሳሪያ ይፈተሻሉ፡፡

5. <u>በዕቃ መፈተሻ መሳሪያ ፍተሻ የማይደረግባቸው ዕቃዎች</u>

የሚከተሉት ዕቃዎች በዕቃ መፈተሻ መሳሪያ ፍተሻ አይደረግባቸውም፤

ሀ/ ማናቸውም በህይወት ያሉ እንስሳት፤

ለ/ በኮንቴይነር ያልታሸጉ እና የሥጋት ደረጃቸው ዝቅተኛ የሆኑ ዕቃዎች፣

ሐ/ሌሎች የባለሥልጣኑ መስሪያ ቤት በሚያወጣው ሰርኩላር ከፍተሻ ነፃ የሚደረጉ ዕቃዎች ፤

6. <u>የመፈተሻ ቦታ /ጣቢያ/</u>

1. የዚህ መመሪያ የአንቀፅ 5 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ አገር የሚገቡ ወይም ከአገር የሚወጡ ማናቸውም ዕቃዎች በጉምሩክ መውጫና መግቢያ በሮች እንዲሁም በመተላለፊያ መንገዶች ላይ በተተከሉ የዕቃ መፈተሻ መሳሪያዎች በሚገኙበት ሥፍራ ይፈተሻሉ::

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ቢኖርም አንድ ጊዜ ፍተሻ የተደረገበት ዕቃ አስገዳጅ ወይም አስፈላጊ ሁኔታ አለ ካልተባለ በስተቀር በድጋሚ በሌላ ጣቢያ በመሳሪያ ፍተሻ አይደረግበትም::

7. <u>በፍተሻ ወቅት ስለሚገኝ ልዩነት</u>

1. በመሳሪያ በተደረገ ፍተሻ ልዩነት የተገኘባቸውን ዕቃዎች በተመለከተ ልዩነቱን ያገኘው ቅ/ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ የፍተሻ ውጤቱን ከዝርዝር መግለጫ ጋር ዕቃውን አሳጅቦ ዲክላራሲዮን ለተከፈተበት ጣቢያ ያስተላልፋል::

2. ዲክላራሲዮን የተከፈተበት ጣቢያም የተላለፈለትን የፍተሻ ውጤትና መግለጫ መሠረት በማድረግ ዕቃው ሙሉ በሙሉ እንዲፈተሽ በማድረግ የተባለው ልዩነት መኖሩን ካረጋገጠ በጉዳዩ ላይ እንደሁኔታው በአስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲታይ ወይም በወንጀል ምርመራ እንዲጣራና በፍ/ቤት/ ተገቢው ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል::

3. በመሳሪያ የተደረገ ፍተሻ ልዩነት ያልተገኘበት ስለመሆኑ ወይም ልዩነት የተገኘበት ስለመሆኑ ያለአግባብ የተሰጠ የተሳሳተ ማስረጃ የተገኘ እንደሆነ ማስረጃ የሰጠው ኦፊሰር ወይም ኃላፊ በአዋጁና በሠራተኛ መተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ተገቢው ህጋዊ እርምጃ ይወሰድበታል::

## ክፍል ሦስት

## ስለአካላዊ የዕቃ ፍተሻ

8. መርህ

በዚህ መመሪያ መሠረት በዕቃ መፈተሻ መሳሪያ ያልተፈተሹ ዕቃዎች ወይም በመሳሪያው ተፈትሸው ልዩነት የተገኘባቸው ወይም ጥቆማ ወይም መረጃ የቀረበባቸው ማናቸውም ገቢና ወጪ ዕቃዎች የሥጋት ሥራ አመራርን መሠረት በማድረግ አካላዊ የዕቃ ፍተሻ ይደረግባቸዋል፡፡

9. በናሙና ስለሚፈተሹ ዕቃዎች

1. በሥጋት ሥራ አመራር የሥጋት ደረጃቸው ቀይ የሆኑ ወይም የሥጋት ደረጃቸው ቢጫ ሆነው ወደ ቀይ የተለወጡ ዕቃዎች ስታንዳርድ ዝርዝር የዕቃ መግለጫ ሰነድ ከቀረበላቸው ዕቃዎች በዓይነታቸው ተለይተው ከተደረደሩ በኋላ ከተመሳሳይ የዕቃዎች ጥቅል ላይ አጠቃላይ ጭነቱን እንዲወክል በማድረግ በሚከተለው ሁኔታና ስኬል መሠረት ናሙና እየተወሰደ ፍተሻው ይከናወናል፡፡

   ሀ. ከ1 እስከ 20 ጥቅል ከሆኑት፣4 ጥቅል ናሙናዎችን፤

   ለ. ከ21 እስከ 40 ጥቅል ከሆኑት፣ 8 ጥቅል ናሙናዎችን

   ሐ. ከ41 እስከ 60 ጥቅል ከሆኑት፣12 ጥቅል ናሙናዎችን፤

   መ. ከ61 እስከ 80 ጥቅል ከሆኑት፣16 ጥቅል ናሙናዎችን

   ሠ. ከ81 እስከ 100 ጥቅል ከሆኑት፣ 20 ጥቅል ናሙናዎችን፤

   ረ. ከ100 ጥቅል በላይ ከሆነ በእያንዳንዱ ተጨማሪ መቶ ጥቅል ላይ 20 ጥቅል ናሙናዎችን በመውሰድ ፍተሻው ይከናወናል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ የተጠቀሰው ቢኖርም በመጀመሪያ ከተወሰዱት ናሙናዎች በተደረገ ፍተሻ ልዩነት ከተገኘ ወይም ለዕቃዎቹ የቀረበው ስታንዳርድ ዝርዝር የዕቃ መግለጫ ሰነድ መሠረት ካልሆነ በዲክላራሲዮኑ በተመዘገቡት ዕቃዎች ላይ ሙሉ በሙሉ ፍተሻ ይከናወናል፡፡ ሆኖም በናሙና ፍተሻ የተገኘው አነስተኛ ነው ተብሎ በጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ሥራ ሂደት መሪው ሲታመን ልዩነቱን ለማረጋገጥ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት በተመሳሳይ ናሙና በመውሰድ ፍተሻ ማድረግ ይቻላል፡፡

3. የናሙና አወሳሰድ በኮምፒውተር ሲስተም አማካኝነት ተፈፃሚ እንዲሆን ባለስልጣኑ የሚዘረጋው አሰራር ተፈፃሚነት ይኖረዋል::

10. <u>ድንገተኛ ፍተሻ</u>

1. ባለሥልጣኑ ወደ ሀገር በሚገቡ፣ ከሀገር በሚወጡ ወይም በተሳሳፊ ዕቃዎች ሳይ በሥራ ሳይ ባለው የሥጋት ሥራ አመራር መርህ እና በተጨባጭ መረጃ ሳይ በመመስረት ከሚያደርገው መደበኛ ፍተሻ ወጭ ዕቃዎችን በድጋሚ ሲፈትሽ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የሚደረገው ድንገተኛ ፍተሻ የሥጋት ደረጃቸው ዝቅተኛ በሆኑ ዕቃዎች እንደዚሁም ሰዎች ሳይም ተፈፃሚ ሲሆን ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀፅ መሰረት የሚደረግ ድንገተኛ ፍተሻ አስቀድሞ በተደረገ ዝግጅት ወይም ዕቅድ መሰረት ተፈፃሚ መሆን አለበት፡፡

4. በተደረገው ድንገተኛ ፍተሻ ልዩነት የተገኘ እንደሆነ እና አስቀድሞ በተደረገው ፍተሻ ይኸው ልዩነት ያልተገለፀ እንደሆነ አስቀድሞ ፍተሻውን ያከናወነው ወይም ያከናወኑት ኦፊሰሮች በአዋጁና በሠራተኛ መተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

5. በድጋሚ በሚደረግ ፍተሻ የሚገኝ ልዩነት አስቀድሞ በአግባቡ በተወሰደ ናሙና ሳይ ሳይሆን በናሙና ባልተወሰዱ ዕቃዎች ሳይ የሚገኝ ልዩነት ከሆነ ፍተሻውን ባከናወነው ወይም ባከናወኑት ሠራተኞች ሳይ ኃሳፊነት አያስከትልም፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የውጭ ፍተሻ</u>

11. <u>የውጭ ፍተሻ ስለሚፈቀድበት ሁኔታ</u>

በዚህ መመሪያ መሠረት የውጭ ፍተሻ እንዲፈቀድለት የሚጠይቅ ሰው ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዘውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙሳት እና አስፈሳጊ ሰነዶችን በማያያዝ ዲክለራሲዮን ለተከፈተበት ቅ/ጽ/ቤት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

12. <u>የውጭ ፍተሻ የመፍቀድ ኃላፊነት</u>

የውጭ ፍተሻ ፈቃድ የሚሰጠው ዲክላራሲዮን በተከፈተበት የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች ሲሆን፤

1. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 13 መሠረት የሚጠየቅ የውጭ ፍተሻን የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም የሥራ ሂደት መሪው ወይም እሱ በሚወክለው ሰው የውጭ ፍተሻ ፍቃድ ይሰጣል፡፡
2. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 13 ከተዘረዘሩት ድርጅቶችና ዕቃዎች በተጨማሪ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ልዩ እና አሳማኝ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ ለቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ የውጭ ፍተሻ ጥያቄ ሲቀርብና ፈቃድ ሲሰጥ ይችላል፡፡ በልዩ ሁኔታ በሥራ አስኪያጅ ብቻ የተፈቀደ የውጭ ፍተሻን በተመለከተ መረጃዎቹ ተለይተው መያዝ አለባቸው፡፡

13. <u>የውጭ ፍተሻ የሚፈቀድላቸው ድርጅቶች እና ዕቃዎች</u>

1. ከባለሥልጣኑ ጣቢያ ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ውጭ ፍተሻ እንዲደረግ የሚፈቀድላቸው ድርጅቶች እና ሰዎች፤

   ሀ. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና የመንግሥት አክሲዮን ያላቸው ድርጅቶች፤

   ለ. የወጪ ንግድ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ ግለሰቦችና ድርጅቶች፤

   ሐ. የፕሮጀክትና የመንገድ ሥራ ተቋራጭ ድርጅቶች፤

   መ. የልማት ማህበራትና በነዚሁ የተቋቋሙ ተቋማት፤

2. ከባለሥልጣኑ ጣቢያ ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ውጭ ፍተሻ እንዲደረግ የሚፈቀድላቸው ዕቃዎች፤

   ሀ. የፋብሪካ ጥሬ ዕቃዎችና ኬሚካሎች እንዲሁም የተቀጣጣይነት ባህሪ ያላቸው ዕቃዎች፤

   ለ. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ወይም የመንግሥት ድርጅቶች የሚያስመጧቸው ዕቃዎች ፤

   ሐ. ነዳጅ እና የነዳጅ ውጤቶች፤

   መ. ለፍተሻ አመቺ ያልሆኑ ትላልቅ የፋብሪካ ማሽነሪዎች፤

   ሠ. በአንድ አስመጪ በአንድ ጊዜ የሚመጡ እና ቁጥራቸው ከ10 በላይ የሆኑ አዳዲስ ተሽከርካሪዎች፤

   ረ. ማዳበሪያ፣የእርዳታ እህል እና ሌሎች ከዚሁ ጋር በተያያዘ በብዛት መጥተው ወደብ ላይ የሚታሸጉና ወደ ሀገር የሚጓጓዙ መሰል ዕቃዎች፣

ሰ. የወጪ ዕቃዎች፤

ሸ. ለፍተሻ አመቺ ያልሆኑ የኢንቨስትመንት ዕቃዎች፤

ቀ. የልማት ማህበራት የሚያስመጧቸው እና ለማራገፍና ለመጫን ወይም ለመፈተሽ አመቺ ያልሆኑ ዕቃዎች ፤

3. በዚህ አንቀፅ ከተዘረዘሩት ጋር ተመሳሳይ ወይም ተወዳዳሪ ናቸው በሚል በቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ የውጭ ፍተሻ የሚፈቀድላቸው ዕቃዎችና ድርጅቶች ናቸው::

14. <u>የውጭ ፍተሻ ስለመፍቀድ</u>

1. ባለሥልጣኑ ወደ አገር በሚገቡ ወይም ከአገር በሚወጡ ዕቃዎች ዲክላራሲዮን ከቀረበበት የጉምሩክ ጣቢያ ወይም ቅ/ጽ/ቤት ውጭ በሚገኙ ቦታዎች፣ ድርጅቶች፣ መጋዘኖች፣ በፕሮጀክት ሳይቶች ሳይ፤ ወይም እንደአስፈላጊነቱ በሌላ ቦታ የውጭ ፍተሻ እንዲደረግ ሲፈቀድ ይችላል::

2. ቅ/ጽቤቱ ተጨባጭ መረጃን ወይም ጥቆማን መሠረት በማድረግ፣ ወይም በልዩ ሁኔታ ለቀረቡ ጥያቄዎች አሳማኝ ምክንያት ያልቀረበ መሆኑን መሠረት በማድረግ የውጭ ፍተሻ ሳይፈቅድ ይችላል::

3. የውጭ ፍተሻ ዲክላራሲዮን ከተከፈተበት ጣቢያ ውጪ በሚገኙ ጣቢያዎችና ከጉምሩክ ጣቢያ ውጪ በሚገኙ ቦታዎች የሚጠየቅ ሲሆን የውጭ ፍተሻ እንዲደረግ ሳይፈቀድ ይችላል::

15. <u>የውጭ ፍተሻ የሚያደርግ ጣቢያ ወይም ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊነት</u>

1. በዚህ መመሪያ መሠረት የውጭ ፍተሻ የሚያደርግ የጉምሩክ ጣቢያ ወይም ቅ/ጽ/ቤት የፍተሻውን ውጤት ለፈቀደው ቅ/ጽ/ቤት ፍተሻው በተጠናቀቀ በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ በፋክስ ማሳወቅ አለበት፤

2. ኦርጂናል የፍተሻ ውጤቱንም ፋክስ ባደረገበት ዕለት ለፓስታ ቤት በማስረከብ በ20 የሥራ ቀናት ውስጥ ለፈቀደው የቅ/ጽ/ቤት እንዲደርስ ማድረግ አለበት፤

3. የውጭ ፍተሻ የፈቀደው ቅ/ጽ/ቤትም በደረሰው ሪፓርት መሠረት አስፈላጊው ሥርዓት መፈፀሙን በማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ ዲክላራሲዮን መዝጋትን ጨምሮ ቀሪ ሥራዎችን ያከናወናል::

4. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7(3) ወይም አንቀፅ 10(5) መሠረት የተፈፀመ ጥፋትና የተወሰደ እርምጃ ቢበዛ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለዋና መ/ቤቱ በሪፓርት መገለፅ አለበት፡፡

16. <u>የውጭ ፍተሻ አፈፃፀምና ዲክላራሲዮን የተከፈተበት ጣቢያ ኃላፊነት</u>

1. በውጭ የሚደረግ ፍተሻ በዚህ መመሪያ ክፍል ሁለት በተመለከተው ሥርዓት መሠረት የአካል ፍተሻ ይፈፀምበታል፡፡

2. ዲክላራሲዮን የተከፈተበት ጣቢያ የውጭ ፍተሻ በሚደረግበት ጊዜ የሚገኝ ልዩነትን በሚደርሰው የፍተሻ ውጤት እና ይህንኑ በማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ በአስተዳደራዊ ወይም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕጉ መሠረት በፍርድ ቤት ጉዳዩ እልባት እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ስለአገልግሎት ክፍያ</u>

17. <u>የዕቃ ፍተሻ አገልግሎት ክፍያ</u>

1. በዚህ መመሪያ መሠረት በዕቃ መፈተሻ መሳሪያ የሚፈተሹ ዕቃዎች በሙሉ በዕቃዎቹ የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ 0.07 በመቶ (ዜሮ ነጥብ ዜሮ ሰባት) የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላሉ፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ የተገለፀው የአገልግሎት ክፍያ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዕቃዎች አይመለከትም፡፡

ሀ/ በወጪ ንግድ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆኑ ዕቃዎችን፤

ለ/ የወጪ ዕቃዎችን፤

ሐ/ ኤምባሲዎች፣አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች የሚያስገቧቸው ዕቃዎችን፤

መ/ የመንግሥት መ/ቤቶች የሚያሰመጧቸው ዕቃዎችን፤

3. ሆኖም በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2/ሀ/ የተጠቀሱት ዕቃዎች በተለያዩ ምክንያት ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው የሆነ እንደሆነ ዕቃዎቹ ወደ አገር ሲገቡ በነበረው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ 0.07 በመቶ (ዜሮ ነጥብ ዜሮ ሰባት) የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፡፡

18. <u>የአገልግሎት ክፍያ የሚሰበሰብበት ቦታና ሁኔታ</u>

1. ለዕቃ ፍተሻ አገልግሎት የሚከፈለው ክፍያ ለዕቃው ቀረጥና ታክስ በሚከፈልበት ጊዜ እና ቦታ ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት የተሰበሰበው የአገልግሎት ክፍያ በተለየ የገቢ ኮድ እየተመዘገበ አገልግሎቱን ለማስፋፋት ሥራ እንዲውል ይደረጋል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

19. <u>ለህዝብ ስለማሳወቅ</u>

ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 18/1/ መሠረት ስለሚያስከፍለው የዕቃ ፍተሻ አገልግሎት ክፍያ እና ክፍያው ስለሚጀመርበት ጊዜ ለህዝብ ያሳውቃል፡፡

20. <u>ስለተሻሩ መመሪያዎች</u>

የዕቃ ፍተሻ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 14/2001 እንደዚሁም ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ ከዕቃ ፍተሻ ጋር የተያያዙ እና ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም መመሪያዎች፣ ሰርኩላሮች ወይም/ እና ልማዳዊ አሠራሮች በሙሉ በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

21. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የጉምሩክ ዲክላራሲዮን የቀረበባቸውና ተቀባይነት ያገኙ ዕቃዎች በተጀመሩበት ሁኔታ ፍፃሜ ያገኛሉ፡፡

22. <u>መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ-------------------ቀን 2002 ዓ.ም

መላኩ ፈንታ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ዋና ዳይሬክተር